# የሕዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ ጥሪ

**በዋሽንግተን ዲሲ ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን፣**
**ስለ እረፍት ቀናት የባቡርና የሜትሮ አውቶብሶች አገልግሎትና የስምሪት ጊዜ ለውጥ**
**እንዲሁም በአናኮስትያ የአውቶብስ መሳፈሪያ ላይ ልዩ የዋጋ ጭማሪ ለማድረግ የቀረበ**

**ረቂቅ ሰነድ B11-02**

<u>**ዓላማ**</u>

**የዋሽንግተን ዲሲ ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን፣ ባቀረባቸው በእነዚህ ለውጦች ላይ የሕዝብ አስተያየቶችን ለመቀበል በሚከተሉት ቀናትና ቦታዎች ስድስት የህዝብ አስተያየት መስሚያ መድረኮችን (ሂሪንግ - Hearing) አዘጋጅቷል።**

<u>Hearing No. 556</u>
ሰኞ ሜይ 16
ትሪቶፕስ ፕሮፌሽናል ፕሌስ- ኦዲቶሪየም
8181 Professional Place
Hyattsville, MD

<u>Hearing No. 557</u>
ማክሰኞ ሜይ 17
በጆርጅ ዋሽንግተን ሚድል ስኩል ኦዲቶሪየም
1005 Mt. Vernon Ave
Alexandria, VA

<u>Hearing No. 558</u>
ማክሰኞ ሜይ 17
ሴይንት ሜሪስ አርመኒያን አፓስቶሊክ ቸርች
ፌሎውሺፕ ሆል
4125 Fessenden St, NW
Washington, DC

<u>Hearing No. 559</u>
ረቡዕ ሜይ 18
አርሊንግተን ካውንቲ ቦርድ ሩም 3ኛ ፎቅ
2100 Clarendon Blvd
Arlington, VA

<u>Hearing No. 560</u>

ረቡዕ ሜይ 18
ፈርስት ባብቲስት ቸርች ኦፍ ዊተን
ፌሎው ሺፕ ሆል
10914 Georgia Ave
Wheaton, MD

Hearing No. 561
ሐሙስ ሜይ 19
ማቲው ሜሞሪያል ባብቲስት ቸርች
John H. Kearney, Sr. Fellowship Hall
2616 Martin Luther King Jr Ave, SE
Washington, DC

በ5:30 pm ጀምሮ ለህዝብ ክፍት ይሆናል በ6 p.m. ህዝባዊ ስብሰባ ይደረጋል በ6:30 pm የህዝብ አስተያየት መስማት ይጀምራል

የህዝብ አስተያየት የሚሰማባቸው ቦታዎች በሙሉ ዊልቼር መጠቀም ይቻላል። ልዩ እርዳታ፣ ወይም የምልክት ቋንቋን መጠቀም የሚሹ፣ ወይም አስተርጓሚ የሚፈልጉ ፣ወይንም ይህንን መረጃ በተለየ መልኩ እንዲደርሳቸው የሚፈልጉ ሁሉ ዴኒስ ፔና ን በ202- 962 -2511 ማነጋገር ይችላሉ። መስማት የተሳናቸው በ202- 638-3780 ሌሎች የአስተርጓሚ ወይም የቋንቋ ነክ እርዳታዎችን የሚሹ ደግሞ በ202-962-1082 መደወል ይችላሉ።

ለበለጠ መረጃ www.wmata.com/hearings መመልከት ይቻላል።

## ረቂቅ ፕሮፖዛል-

ላለፉት ዓመታት ሜትሮ ራሱን መልሶ በማነጽ በርካታ ለውጥና መሻሻሎችን አሳይቷል። በተለይም የሚሰጠውን አገልግሎት በማሻሻል፣ ደህንነቱን በመጠበቅ፣ የተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት በመንገባት ውጤት አስገኝቷል። አስተማማኝ ኢንቨስትመንት ስትራቴጂ በመከተልና የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ የብሔራዊ ትራንስፖርት የደህንነት ቦርድ (National Transportation Safety Board) ቦርድ ያወጣቸውን መስፈርቶች በማሟላት፣ አዳዲስ ተሽከርካሪዎችን፣ የቆዩ የባቡር ሐዲድና የአውቶብስ ኢንፍራስትራክቸሮችን አሻሽሏል። ዘላቂነትና ዘመናዊነቱን ይዞ እንዲጓዝ የሚያስችሉትን ሁሉ በማሻሻል አስተማማኝ ሥርዓት ዘርግቷል።

ራሱን መልሶ በመገንባት ሂደትም ውስጥ በታሪኩ ውስጥ ከፍተኛ የሆነውን የካፒታል ፕሮግራም በማካሄድ ላይ ነው። ለ2012 የበጀት ዓመት የቀረበው የ$1.5 ቢሊዮን የሥራ ማስኬጃ በጀት ለመልሶ ማቋቋሚያና ማጠናከሪያ ፕሮጀክቶቹ እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ለሜትሮ ወሳኝ የሆኑት የአውቶቡስ፣ የባቡሮችና ተያያዥ የመሸጋገሪያና መጓጓዣ አገልግሎቶች የዋጋ ጭማሪ ሳይደረግባቸው አገልግሎታቸውን በጥራት እንዲሰጡ የሚያስችል ነው።

ከዚህ የበጀት ካፒታል ጎን ለጎን ሜትሮ ወጪዎቹን በመቆጠብ አላስፈላጊ የሆኑትን ፕሮግራሞች በመቀነስና በማቋረጥ አንዳንዶቹንም በዘመናዊ መሣሪያዎች እንዲተኩ በማድረግ $165 ሚሊዮን ዶላር አድኗል።

በሚቀጥለውም ዓመት ለደንበኞች የሚሰጠውን የአገልግሎት ጥራት ሳይቀንስ ለአካባቢው ኢኮኖሚ ጉልህ ድርሻ ያላቸውንና የክልሉ ነዋሪ የሆኑ ሠራተኞችንም ሳይቀንስ $74.2 ሚሊዮን የሚሆን ገንዘብ ከሥራ ማስኬጃ በጀት ላይ በመቀነስ ለማዳን አቅዷል።

ባለፈው ዓመት፣ ሜትሮ የሚሰጠውን አገልግሎት ከሚያቋርጥ እኛ ለሜትሮ  የበኩላችንን ድጋፍ መስጠት እንመርጣለን ያሉ  ደንበኞቹ ባሳዩት የሞራል ድጋፍ ሜትሮ ያደረገውን የዋጋ ጭማሪ በጸጋ ተቀብለዋል። ይህም በመሆኑ በሚቀጥለው ዓመት ሜትሮ ከተደረጉት የተለያዩ ጭማሪዎች በድምሩ $700 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ያገኛል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ሆኖ ሜትሮ በርካታ አስተዳደራዊ ማስተካካያዎችን ቢያደርግም ተያያዥ ለሆኑ የተለያዩ ወጪዎች መዳረጉ አልቀረም። ያልተጠበቁ የሠራተኛ ወጪዎችና ጥቅማጥቅሞች ከሜትሮ ጋር ከተገናኙ ሌሎች የአገልግሎት ዘርፎችና ሲወራረሱ ከመጡ እዳዎች ጋር ተዳምረው ብዙ ወጪዎች መኖራቸው ይታወቃል። ሜትሮ እነዚህን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚሰጠውን አገልግሎት ሳይቀንስ የተሻለ አገልግሎት እየሰጠ ለመቀየት የ$66 ሚሊዮን ዶላር ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልገዋል። ከዚህ ዶክመንትም ጋር ተያይዞ እንደተመለከተው የተለያዩ ክፍሎችን እርዳታና ድጋፍ እንዲሁም መጠነኛ የዋጋ ማሻሻያ ማድረግን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ ከ2012 የበጀት ዓመት በክፊል የሚታሰበውን የ$5.3ሚሊዮን ዶላር አካቶ በዓመት $7ሚሊዮን ዶላር ይጠበቃል።  በመሆኑም ከህዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ መድረኩ የሜትሮ አውቶብስና የሜትሮ ባቡሮችን አገልግሎትን በጀትና ማሻሻያ አስመልክቶ ከዚህ በታች ተዘርዝሮ በቀረበው የ2012 በጀትና ማስተካከያ ላይ የህዝብ አስተያየት ይጠበቃል።

**በአውቶብስ አገልግሎት (Bus Service-)**

1. የ E6, K1 and N8 መስመሮችን ማቋረጥ

2. የ M4 አቅጣጫ ወደ ኖልውድ ሪታይርመንት ሆም ድረስ በማስረዘም የ E6 መስመርን በከፊል መተካት

3. በሲልቨር ስፕሪንግ እና በአርካይቭ መካከል ያለውን የ70 እና 71 ቁጥር መስመርን ማሳጠርና በረሽ ሀወር ሰዓት ያለውን ምልልስ ቁጥር መቀነስ። በሥራ  ቀናት ከማለዳው 11 ሰዓት  እስከ ምሽቱ 2ሰዓት (5 AM and 8 PM.) በFort McNair/Buzzard Point and Gallery Place — Chinatown መካከል አዲስ የ74 ቁጥር መስመር መዘርጋት በምሽትና በእረፍት ቀናት የ V8ን መስመር በFort McNair በመቀየር ወደ Gallery Place - Chinatown ማርዘም። V7ን በሥራ ቀናት ከምሽቱ 2 (8 PM) በኋላ ያለውን ስምሪት ማቋረጥ።

4. የአናኮስትያን ልዩ ዋጋ ማቋረጥ የ94, A2, A4, A5, A6,A7, A8, M8, M9, W2, W3, W6 እና W8 መስመሮች እንዲሁም በ south of Good Hope Road ላሉት  90, B2, P1, P2, P6 and U2. መስመሮች መሳፈሪያ ዋጋ ለስማርት ትሪፕ ከ$1.00 ወደ $1.50 ለካሽ ደግሞ $1.70 መቀየር

5. በተራ ቁጥር 5 ከተጠቀሱት የዋጋ ጭማሪዎች ጋር ተግባራዊ የሚሆኑ በ94, A2, A4, A5, A6, A7, A8, M8, M9, W2, W3, W6 እና W8 መስመሮች ላይ  ከአውቶብስ ወደ ሜትሮ ከሜትሮ ወደ አውቶብስ ያሉትን የዋሽንግተን ዲሲ መንግሥት በደንብ ቁጥር 79 ያወጣውን ደንብ በማይቃረን መልኩ ከ$0.50 ወደ $1.00 ከፍ ማድረግ

**የባቡር አገልግሎት (Rail Service)**

• ቅዳሜ ቅዳሜ እስከ 9:30 PM ድረስ በተከታታይ በባቡሮች መካከል ያለውን የ12 ደቂቃ የቆይታ ክፍተት ወደ 18 ደቂቃ ከ9:30 PM በኋላ እስከ እለቱ የሜትሮ አገልግሎት ማብቂያ ሰዓት ድረስ ደግሞ ወደ 25 ደቂቃ ከፍ ማድረግ

• የእሁዱንም እንደዚሁ እስከ 9:30 PM ድረስ በተከታታይ ባቡሮች መካከል ያለውን የ15 ደቂቃ ቆይታ ወደ 20 ደቂቃ ከፍ ማድረግ ከ9:30 PM በኋላ ደግሞ እስከመጨረሻው ድረስ ወደ 25 ደቂቃ ማራዘም

## Paratransit Service

• ደንበኞች በየሜትሮ ትራንስፖርት አገልግሎቶች አጠቃቀም ንዑስ 4 ላይ በተጠቀሰው ቋሚ መስመርና ዋጋ ዝርዝር መሠረት አሁን የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ $2 ዶላር ነው። አሁን የቀረበው የአናኮስትያ ልዩ ዋጋ ማሻሻያ ተግባራዊ ከሆነ የሚከፍሉት $3.00 ዶላር ይሆናል።

በስምሪት መስመሮችና በዋጋ ጭማሪው ላይ የሚደረገው ለውጥ ተግባራዊ እንዲሆን የታሰበው ከሰፕቴምበር 25 ቀን 2011 ጀምሮ ነው። በዚህ ፅሑፍ ያልተጠቀሱትን ጨምሮ፣ የበጀት ጉድለቱን አስመልክቶ ስለቀረቡ የመፍትሔ ሀሳቦች ሙሉ ዝርዝር በ www.wmata.com በሚለው ድህረ ገጽ መመልከት ይቻላል።

ፖሊሲው (በsection 62 of the WMATA Compact,) በሚያዘው መሠረት ሜትሮ ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን 6 የህዝብ አስተያየት ማሰባሰቢያ መድረኮችን (ሂሪንግ) ያዘጋጃል። ስለ አስተያየት አሰጣጡና መድረኮቹ (ሂሪንግ) ያሉት መረጃዎች በየአካባቢው ቤተመጻህፍት (ላይብረሪዎች) በሜትሮ አውቶብሶችና ባቡሮች እንዲሁም በ www.wmata.com/hearings. ይፋ ይደረጋሉ።

<u>በመድረኩ (ሂሪንግ) ቀርቦ ለመናገር መመዝገብ የሚቻለው እንዴት ነው? (HOW TO REGISTER TO SPEAK?)</u>

በቀረበው ሰነድ ላይ አስተያየታቸው እንዲደመጥ የሚፈልጉ ተጨማሪ ሀሳብም ሆነ ሌሎች አማራጮችን ለማቅረብ ለሚሹ ድርጅቶች ሆነ ግለሰቦች በሙሉ እድሉ ይሰጣቸዋል። አስተያየታቸውን መስጠት የሚፈልጉ ዜጎችም ሆነ የድርጅት ተወካዮችም ከሆኑ የድርጅቱን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥርና ቀርበው መናገር የሚፈልጉበት ቀንና ቦታ ለይተው በ600 Fifth Street,NW, Washington, D.C. 20001 ለሚገኘው የዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን ጽ/ቤት ማሳወቅ አለባቸው። ወይም በኢሜይል speak@wmata.com. መላክ ወይንም በ202-962-1133 ፋክስ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እነዚህ መረጃዎች በዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን (Public Access to Records Policy (PARP) መሠረት) በ wmata.com/about_metro/public_rr.cfm ዌብ ሳይት ቀርበው ለህዝብ ክፍት ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ መኖሩን ማወቅ ያስፈልጋል። በእያንዳንዱ ቅጽ ላይ የአስተያየት መስሚያ መድረኩን ማመሳከሪያ (ሂሪንግ ሪፈረንስ) ቁጥርና የአንደኛውን ተናገሪ ስም ብቻ መመዝገብ ይበቃል። የተናጋሪዎችን ስም ዘርዝሮ መጻፍ ተቀባይነት አይኖረውም። ለመናገር የተመዘገቡት ከተናገሩ በኋላ ምናልባት ሌሎች ሊናግሩ የሚችሉበት እድል ሊኖር ይችላል። የመንግሥት ባለሥልጣናት በቅድሚያ ለ5ደቂቃ ያክል ብቻ ከተናገሩ በኋላ ሌሎች አስተያየት ሰጪዎች እያንዳንዳቸው ለሶስት ደቂቃ ያክል ይናገራሉ። በተናጋሪዎች መካከል ደቂቃ መዋዋስም ሆነ ማስተላለፍ አይፈቀድም።

## <u>በጽሑፍ የሚቀርቡ አስተያየቶችን እንዴት ማቅረብ ይቻላል? (HOW TO SUBMIT WRITTEN STATEMENTS?)</u>

በጽሑፍም ሆነ በአሰረጅነት የሚቀርቡ አስተያየቶች እስከ ማክሰኞ ሜይ 24/2011 ከሰዓት በኋላ 5 p.m ድረስ ብቻ  የዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን ጽ/ቤት መድረስ ወይም በ writtentestimony@wmata.com ኢሜይል አድራሻ ወይም በ 600 Fifth Street, NW, Washington, DC 20001 በኩል ለየዋሽንግተን ሜትሮ ትራንዚት ባለሥልጣን ጽ/ቤት መላክ አለባቸው። በ202 962-1133 ቁጥርም ፋክስ ማድረግ ይቻላል። በእያንዳንዱ ደብዳቤ ላይ የአስተያየት መስሚያ መድረኩን ማመሳከሪያ (ሂሪንግ ሪፈረንስ) ቁጥር B11-02 መጥቀስ ያስፈልጋል። በአስተያየቱ ላይ የሚሰጡ ስሞችም ሆኑ የኢ ሜይል አድራሻዎችን የ(WMATA Public Access to Records Policy) በሚፈቅደው መሠረት ከላይ በተጠቀሰው ዌብሳይት ለህዝብ ሊገለጹ የሚችሉበት አግባብ ይኖራል።

ከዚህም በተጨማሪ የሜትሮን የበጀት ጉድለት ለሟሟላት የህዝብ አስተያየት በሚሰበሰብበት በhttp://survey.wbanda.com/budgetsurvey ዌብሳይት ድምፅም ሆነ ተጨማሪ አስተያየት መስጠት ይቻላል። የዌብ ሳይቱ አስተያየት በአካል ቀርቦ (በሂሪንግ) ከሚሰጠው በተጨማሪ ሲሆን ዌብ ሳይቱ ላይ የተጠቀሰው አድራሻም ሆነ ኢንፍሮሜሽን ለማንም አይገለጽም። ዌብ ሳይቱ ሰኞ ሜይ 9 ድረስ 5 ሰዓት 5 p.m. ጀምሮ እስከ ዓርብ ሜይ 20/2011 እኩለ ቀን ድረስ ለህዝብ ክፍት ሆኖ ይቆያል።